# ትምህርት 49

1. መጥምቁ ዮሐንስ የአይሁዶችን ልብ የሚያዘጋጀው ለማን ነበር?
ሀ- ለአዳኙ ለኢየሱስ።

2. መጥምቁ ዮሐንስ የአይሁዶችን ልብ የሚያዘጋጀው እንዴት ነው?
ሀ- የእግዚአብሔርን ቃል ለእነርሱ በማስተማር።

3. መጥምቁ ዮሐንስ አይሁዶችን ምን አስተማራቸው?
ሀ- መጥምቁ ዮሐንስ አይሁዶች ንስሐ መግባት እንዳለባቸው አስተማራቸው።

4. «ንስሐ መግባት» ምንድን ነው?
ሀ- ንስሐ መግባት ስለ እግዚአብሔር ያለንን አስተሳሰብ መቀየር ነው ምክንያቱም እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ ወደ እርሱ መቅረብ የምንችለው በእርሱ መንገድ ብቻ ስለሆነ ነው።
ለ- ንስሐ መግባት ስለ ራሳችን ያለንን አስተሳሰብ መቀየር ነው ምክንያቱም እኛ ሁላችን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ስለሠራን ነው።
ሐ- ንስሐ መግባት ስለ ኃጢአት ያለንን አስተሳሰብ መቀየር ነው ምክንያቱም እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በዘላለም ሞት ስለሚቀጣ ነው።

5. ጥምቀት ምንድን ነው?
ሀ- ጥምቀት ንስሐ ስለመግባታችንና በእግዚአብሔር ብቻ ስለማመናችን የሚገልጽ ምልክት ነው።

6. ጥምቀት ሰውን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ሊያድን ይችላል?
ሀ- አይችልም።

7. አይሁዶችን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ማዳን የሚችለው ማን ብቻ ነበር?

ሀ- አዳኙ ኢየሱስ ብቻ ነበር።

8. መጥምቁ ዮሐንስ ፈሪሳውያንንና ሰዱቃውያንን የእፉኝት ልጆች ብሎ የጠራቸው ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን በጣም ይኮሩ ስለ ነበር ነው።

ለ- ምክንያቱም ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ንስሐ መግባት ስላልፈለጉ ነበር።

9. ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን እግዚአብሔር በእነርሱ ደስ እንደሚሰኝ ያሰቡት ለምን ነበር?

ሀ- ምክንያቱም የእነርሱ ሥራ እግዚአብሔር በእነርሱ እንዲደሰት እንደሚያደርግ ስላሰቡ ነበር።

10. ከምንሠራቸው ሥራዎች እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኘው የሚችል አለ?

ሀ- የለም።

11. እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ብቸኛ ሥራ ምንድን ነው?

ሀ- ስለ ኃጢአት ንስሐ መግባት።

12. ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን እግዚአብሔር በእነርሱ ደስ እንደሚሰኝ ያሰቡት ሌላ ምክንያት ምን ነበር?

ሀ- የአብርሃም ዘር በመሆናቸው።

13. ከአንድ ሰው የዘር ሐረግ መወለዳችን እግዚአብሔርን ሊያስደስተው ይችላል?

ሀ- አይችልም።

14. መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኩራተኞችና ንስሐ መግባት ስለማይፈልጉ ሰዎች ምን አለ?

ሀ- እግዚአብሔር እንደመጥፎ ዛፍ እንደሚቆርጣቸውና በዘላለማዊ የእሳት ባሕር ውስጥ እንደሚጥላቸው ተናገረ።

15. ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ወቅት ይመራው የነበረው ማን ነበር?
ሀ- እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ።

16. ኢየሱስ በተጠመቀበት ወቅት እግዚአብሔር አብ ስለ ኢየሱስ ምን አለ?
ሀ- እግዚአብሔር አብ መሉ በሙሉ በኢየሱስ መደሰቱን ገለጸ።

17. መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን «የእግዚአብሔር በግ» ብሎ የጠራው ለምን ነበር?
ሀ- እግዚአብሔር በይስሐቅ ምትክ እንዲሞት በግ እንዳዘጋጀ ሁሉ ለሰዎች ሁሉ እንዲሞት ኢየሱስን ስለሰጠ ነው።

- መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ካጠመቀው በኋላ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ወደ ምድረ በዳ መራው።

ማቴዎስ 4፡1

1- ከዚህ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን በዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው።

- ኢየሱስ በምድረ በዳ ሳለ ምን ደረሰበት?

- ሰይጣን ኢየሱስን ፈተነው።

- ሰይጣን ማንነቱ አይለወጥም።

- ሰይጣን ከመጀመሪያው ክፉ ነው።

- ሰይጣን አዳምንና ሔዋንን እንደ ፈተናቸው ሁሉ አሁን ደግሞ ኢየሱስን ፈተነው።

- ሰይጣን ኢየሱስን ለምን ፈተነው?

- ምክንያቱም ሰይጣን ኢየሱስ ኃጢአት እንዲሠራ ስለፈለገ።

- ሰይጣን ኢየሱስ ኃጢአት እንዲሰራ የፈለገው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ሰይጣን ኢየሱስ ሰዎችን እንዲያድን ስለማይፈልግ።

- ኢየሱስ ኃጢአት ቢሠራ ኖሮ ሰዎችን ማዳን ይችል ነበር?
- አይችልም።

- ኢየሱስ ኃጢአት ቢሠራ ኖሮ ሰዎችን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ሊያድናቸው አይችልም ነበር።

- ሰይጣን ኢየሱስን የፈተነው አዳኙን አምላክ ኢየሱስን ለማሸነፍ ስለ ፈለገ ነበር።

- ሰይጣን ኢየሱስን የፈተነው ኢየሱስን ባሪያ ሊያደርገው ስለ ፈለገ ነበር።

- ኢየሱስ በምድረ በዳ ለ40 ቀናት ያህል ጾመ።

ማቴዎስ 4፡2

2- አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ፣ ተራበ።

- ኢየሱስ ፍጹም አምላክ ቢሆንም ፍጹም ሰውም ነበር።

- ኢየሱስ የተራበው ለዚህ ነበር።

- ሰይጣን ለኢየሱስ ያቀረበው የመጀመሪያው ፈተና ምን ነበር?

ማቴዎስ 4፡3

3- ፈታኙም ወደ ኢየሱስ ቀርቦ፣ «የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እነዚህን ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ እዘዝ» አለው።

- ሰይጣን ኢየሱስን እንዲህ አለው «የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ። »

- ሰይጣን ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አያውቅም ነበር?
- አዎን።

- ታዲያ ሰይጣን «የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ» ለምን አለው?

- ሰይጣን ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንዲያሳይ እየፈተነው ነበር።

- ሰይጣን ኢየሱስ እግዚአብሔር አብ ያላለውን ነገር እንዲያደርግ እየፈተነው ነበር።

- ሰይጣን ኢየሱስ ከእግዚብሔር አብ ተለይቶ ድንጋይን ወደ ዳቦ እንዲለወጥ እየፈተነው ነበር።

- ኢየሱስ ድንጋዩን ወደ ዳቦ መለወጥ ይችል ነበር?

- አዎን።

- ኢየሱስ እግዚአብሔር ነበር።
- ኢየሱስ ሁሉንም ነገር ማድረግ ይችላል።

- ኢየሱስ ለሰይጣን ምን መልስ ሰጠው?

ማቴዎስ 4፥4

4- ኢየሱስም «'ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል» ሲል መለሰለት።

- ለሰይጣን መልስ ለመስጠት ኢየሱስ ምን አደረገ?

- በእግዚአብሔር መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈውን ቃል ኢየሱስ ለሰይጣን ጠቀሰለት።

- ኢየሱስ ሰይጣንን ከምግብ ይልቅ አስፈላጊ ነገር ምንድን ነው አለ?

- ኢየሱስ ሰይጣንን የእግዚአብሔርን ቃል ማመን ከምግብ ይልቅ አስፈላጊ መሆኑን ነገረው።

- ኢየሱስ መመገብ የለብንም አለ?
- አላለም።

- ኢየሱስ ለመኖር መመገብ እንደሚገባን ያውቃል።
- ኢየሱስ ለሰዎች ሁሉ ምግብን ፈጥሮአል።

- ኢየሱስ እውነተኛ ሕይወት የሚገኘው ከእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ለሰይጣን ነገረው።

- ኢየሱስ ቢራብም እንኳ ድንጋዩን ወደ ዳቦ ያልለወጠው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር አብ እንዲህ እንዲያደርግ ስላልነገረው።

- ኢየሱስ ሰይጣንን አይታዘዝም።

- ኢየሱስ እግዚአብሔር አብን ብቻ ይታዘዛል።

- ሰይጣን ለኢየሱስ ያቀረበለት ሁለተኛው ፈተና ምን ነበር?

ማቴዎስ 4፡5-6

5- ቀጥሎም ዲያብሎስ ኢየሱስን ወደ ቅድስት ከተማ በመውሰድ በቤተ መቅደሱም አናት ላይ አውጥቶ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ ራስህን ወደ መሬት ወርውር፤ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤

6- «እግርህ በድንጋይ እንዳይሰናከል፣ በእጃቸው ያነሡህ ዘንድ፣ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል።»

- ሰይጣን ኢየሱስን በኢየሩሳሌም ውስጥ በሚገኝ ቤተ መቅደስ አናት ወሰደውና ኢየሱስ ከቤተ መቅደሱ አናት ወደታች ራሱን እንዲወረውር ነገረው።

- ሰይጣን ኢየሱስ ከቤተ መቅደስ አናት ራሱን ወደ ታች እንዲወረውር ሲነግረው በእግዚአብሔር መጽሐፍ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ኢየሱስን እንደሚጠብቀው መጻፉን ጠቀሶ ነው።

- ሰይጣን በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ ምን እንደ ተጻፈ ያውቃል?
- አዎን።

- ሰይጣን በእግዚአብሔር መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምን እንደ ተጻፈ ያውቃል።

- ሰይጣን በእግዚአብሔር ቃል ምን አደረገ?

- ሰይጣን ሰዎችን ለማጥመድ የእግዚአብሔርን ቃል አጣመመ።

- ሰይጣን ሔዋንን ለማጥመድ የእግዚአብሔርን ቃል ያጣመመው እንዴት ነበር?

- ሰይጣን ሔዋንን እግዚአብሔር ከከለከለው ዛፍ ብትበላ እንደማትሞት ነገራት።

- ሰይጣን ኢየሱስን ለማጥመድ የእግዚአብሔርን ቃል አጣመመ።

- ሰይጣን እግዚአብሔር አብ ያልነገረውን ነገር እንዲያደርግ ኢየሱስን እየፈተነው ነበር።

- ሰይጣን ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አብ አሳብ ውጭ ከቤተ መቅደሱ አናት ወደ ታች እንዲዘልል ኢየሱስን ፈተነው።

- ኢየሱስ ለሰይጣን ምን ብሎ መለሰለት?

ማቴዎስ 4፡7

7- ኢየሱስም «እንደዚሁም በመጻሕፍት፣ ‘እግዚአብሔር አምላክህን አትፈታተነው’ ተብሎ ተጽፎአል» በማለት መለሰለት።

- ለሰይጣን መልስ ለመስጠት ኢየሱስ ምን አደረገ?

- ኢየሱስ በእግዚአብሔር መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈውን ቃል ለሰይጣን ደገመለት።

- ኢየሱስ እግዚአብሔር አብን መፈታተን እንደማይገባ ለሰይጣን ነገረው።

- እግዚአብሔር አብን መፈታተን የሌለብን ለምንድን ነው?
- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁልጊዜ እውነትን ስለሚናገር ነው።
- ምክንያቱም እግዚአብሔር በፍጹም ስለማይዋሽ ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር በፍጹም የገባውን ቃል ስለማያጥፍ ነው።
- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁልጊዜ የገባውን ቃል ስለሚፈጽም ነው።

- ኢየሱስ ለምንድን ነው ከቤተ መቅደሱ አናት ላይ ያልዘለለው?

- ምክንያቱም እንዲህ እንዲያደርግ እግዚአብሔር አብ ስላልነገረው ነው።

- ኢየሱስ ሰይጣንን አይታዘዝም።

- ኢየሱስ እግዚአብሔር አብን ብቻ ይታዘዛል።

- ሰይጣን ለኢየሱስ ያቀረበለት ሦስተኛው ፈተና ምን ነበር?

ማቴዎስ 4፥8-9

8- እንደገናም ዲያብሎስ ኢየሱስን እጅግ ከፍ ወዳለ ተራራ አወጣው፤ የዓለምንም መንግሥታት ከነክብራቸው አሳየውና፣

9- «ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ» አለው።

- ሰይጣን ኢየሱስን ከፍ ወዳለው ተራራ ወሰደውና የዓለምን መንግሥታትና ክብራቸውን አሳየው።

- ሰይጣን ኢየሱስ ከሰገደለት መላውን ዓለም እንዲቆጣጠር እንደሚሰጠው ነገረው።

- ሰይጣን ለኢየሱስ መላውን ዓለም እንዲቆጣጠር መስጠት ይችላል?
- አዎን።

- ሰይጣን ለኢየሱስ መላውን ዓለም የመቆጣጠር ሥልጣን መስጠት የሚችለው እንዴት ነው?

- ምክንያቱም አዳም ለሰይጣን በታዘዘ ጊዜ ሰይጣን የአዳምና የሰዎች ሁሉ ገዥ ሆኗል።

- ምክንያቱም አዳም ለሰይጣን በታዘዘ ጊዜ፥ ሰይጣን የአዳም፥ የሰዎች ሁሉና የዓለም ሁለ ገዥ ሆኗል።

- ኢየሱስ ለሰይጣን ሰገደለት?
- አልሰገደለትም።

- ኢየሱስ ለሰይጣን ምን መልስ ሰጠው?

ማቴዎስ 4፡10

10- ኢየሱስም «አንተ ሰይጣን ከፊቴ ራቅ! ‘ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ስገድ፤ እርሱንም ብቻ አምልክ’ ተብሎ ተጽፎአልና» አለው።

- ለሰይጣን መልስ ለመስጠት ኢየሱስ ምን አደረገ?

- ኢየሱስ በእግዚአብሔር መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈውን ቃል ለሰይጣን ደገመለት።

- ኢየሱስ ሁላችንም እግዚአብሔርን ብቻ ማምለክ እንዳለብን ተናገረ።

- ኢየሱስ ሰይጣንን በምን አሸነፈው?
- በእግዚአብሔር ቃል።

- ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል አጣምሟል?
- አላጣመመም።

- ኢየሱስ በእግዚአብሔር መጽሐፍ እንደተጻፈው የእግዚአብሔርን ቃል ተናገረ።

- በመጀመሪያ ሰይጣን የእግዚአብሔር የበላይ ለመሆን ፈለገ ሆኖም ግን አልተሳካለትም።

- ከዚያ በኋላ ሰይጣን እኛ ከእግዚአብሔር እንድንለይ አዳምንና ሔዋንን አሳታቸው።

- አዳምና ሔዋን ሰይጣንን ስለሰሙ ሰይጣን የአዳምና የሔዋን እንዲሁም የሰዎች ሁሉ ገዥ ሆነ።

- አሁን ደግሞ ሰይጣን የኢየሱስ ገዥ ለመሆን ሞከረ ሆኖም አልተሳካለትም።
- ከኢየሱስና ከሰይጣን የሚበልጠው ማን ነው?

- ኢየሱስ።

- ኢየሱስ ከሰይጣን የሚበለጠው እንዴት ነው?

- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር ስልሆነ ነው።

- ምክንያቱም በመጀመርያ ሉሲፈርን ፍጹም መልአክ አድርጎ የፈጠረው ኢየሱስ ስለሆነ ነው፥

- ኢየሱስ ሉሲፈርን ፍጹም መልአክ አድርጎ ፈጠረው ይሁን እንጂ ሉሲፈር ኃጢአት በመሥራቱ ሰይጣን ሆነ።

- ኢየሱስ በሰይጣንና በአጋንንቱ ላይ ወደ ፊት ምን ያደርግባቸዋል?

- ኢየሱስ ሰይጣንንና አጋንንቱን ሁሉ በዘላለማዊው የእሳት ባሕር ውስጥ ይጥላቸዋል።

- ኢየሱስ ሰይጣንን ካሸነፈው በኋላ ሰይጣን ለጊዜው ትቶት ሄደ።

ማቴዎስ 4፥11

11- ከዚያም ዲያብሎስ ትቶት ሄደ፤ መላእክትም መጥተው አገለገሉት።

- ሰይጣን ለጊዜው ኢየሱስን ትቶት ሄደ እግዚአብሔርም እንዲያገለግሉት መላእክትን ላከለት።

- ሰይጣን ለጊዜው ኢየሱስን ትቶት ቢሄድም በድጋሚ ኢየሱስን ሊፈትነው ይመጣል።